| 3ኛ ዓመት ቁጥር 29<br>3rd year № 29 | ባሀር ዳር ሰኔ 29 ቀን 1990<br>Bahir Dar, 6th July 1998 |
|---|---|


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| የአንዱ ዋጋ ብር 1.00 | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖ· ሣ· ቁ<br>P. O. Box 312 |
|---|---|---|


| ማ ው ጫ | CONTENTS |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 29/1990 ዓ.ም<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዘላቂ የግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ<br>ገጽ 2 | Proclamation No 29/1998<br>A proclamation to amend the proclamation for the establishmentof sustainable Agriculture and enviromental rehabilitation commission of the Amhara National Regional State<br>Page 2 |

## አዋጅ ቁጥር 29/1990 ዓ.ም
## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዘላቂ የግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዘላቂ ግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 5/1988 ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

## PROCLAMATION No 29/1998
## A PROCLAMATION TO AMEND THE FOR ESTABLISHMENT OF SUSTAINABLE AGRICULUTURE AND ENVIROMENTAL REHABILITATION COMMISSON OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

Where as it is has become necessary to amend proclamation № 5/1995 that provides for the establishment of the sustainable agriculture and environmental rehabilitation commission.

Now therefore, the council of the Amhara National Regional State persuant to sub article 3/1 of Article 49 of the constitution of the region, here by proclaimed as follows.

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሄራዊ ክልል ዘላቂ የግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 29 /1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

በአማራ ብሔራዊ ክልል ዘላቂ የግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 5/1988 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል።

   2. የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰይመው አካል የሚመራና ከተለያዩ አካላት ተውጣጥቶ የሚመሰረት ቦርድ ፤

2. አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

   1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰይመው አካል ........ሰብሳቢ

3. የአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

   1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ፤ ሆኖም ኮሚሽነሩ፤ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከቦርዱ አባላት ግማሹ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ሰኔ 29 ቀን 1990 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

1. <u>**short Title**</u>

This proclamation may be cited as " a proclamation to amend, the proclamation that provides for the establishment of the sustainable agriculture and environmental rehabilitation commission of the Amhara National Regional State No 29/1998

2. <u>**Amendment**</u>

Proclamation No 5/1995 that provides for the establishment of the sustainable agriculture and environmental rehabilitation commission of the Amhara National Regional State is amended as follows.

1. Sub article 2 of article 7 is here by deleted and replaced by the following new sub article 2

   2. A Board established and consisted of different organs, and chaired by person to be assigned by the executive committee of the region.

2. sub article 1 of article 11 is here by deleted and replaced by the following new sub article 1

   1. A person to be assigned by the executive committee of the Amhara National Regional State .....chair person .

3. Sub article 1 of article 13 is here by deleted and replaced by the following new sub article 1.

   1.The meeting of the board shall convene once in every 3 months: How ever, extra ordinery meeting shall be held, at any time, where the chair person of the board, the commissioner, or half of the board member request for so.

3.<u>**Effective Date**</u>

This proclamation shall come in to force on the date of its ratification by the council of the Amhara National Regional State.

Done At Bahir Dar
This 6th Day Of July 1998
The Council Of The Amhara National Regional State